## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ህዳር 13፣ 2000 ዓ. ም.)

## ወያኔ የአየር ኃይል መኮንኖችን ለመደለል ከፍተኛ ወጪ በማድረግ እያዝናና፤ በትግራይ ወጣቶች እየታፈሱ ለእስር እየተዳረጉ መሆኑ፣ በአንድ እስር ቤት ብቻ ከ6 ሺህ በላይ ወጣቶች መታሰራቸው

**ሌላም ዜና እዚህ ተጭነው ያንብቡ**

**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ**

በሠራዊቱ ጥያቄ የተደናገጡት የወያኔ ሹማምንቶች ጦሩን ሊያታልል ይችላል ብለው ያሰቡትን እርምጃ ሁሉ ከመውሰድ ወደ ኋላ ሳይሉ የሀገር ሀብትና ንብረት በሆነው ገንዘብ እንደልባቸው ያለ አንዳች ፍርሐት እየረጩ መሆኑን ሰሞኑን ከወደ መቀሌ የደረሰን ዘገባ አስረዳ።

የሰሜን የአየር ኃይል ምድብ ስር ያሉ የአየር ኃይል መኮንንኖች በመሉ በከፍተኛ ወጪ አክሱምንና ሌሎች ቦታዎችን እንደጎበኙ የተደረገ ሲሆን፣ በዚህ ጉብኝት ላይ ከ440 መኮንኖች በላይ እንደተገኙ ዘገባው ገልጿል።

የሰሜን ምድብ የአየር ኃይል መኮንኖች በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ የውሎ አበል ተመድቦላቸው ምግብና ሆቴል ተይዞላቸው እና መጓጓዣ ቀርቦላቸው የአክሱምን ሐውልት እና በመቀሌ «የትግራይ ሰማዕታትን ሐውልት»ን እንዲጎበኙ የተደረገ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆ የወያኔ ቡድን መኮንኖቹን በአሁኑ ሰዓት እንዲህ በየቦታው እየወሰደ የሚያምነሽንሻቸው በምድር ጦር ውስጥ ባሉ የጦሩ አባላት የተነሳው ጥያቄ ወደ አየር ኃይል አባላት እንዳይዛመት እግረ መንገዱን ትምህርት ለመስጠትና በአሁኑ ሰዓት እየተሠራ ያለውን ጥሩ ጥሩ ነገር ብቻ ግንዛቤ ለማስጨበጥና እነሱም ከዚህ ጉብኝት ሲመለሱ ለበታቾቻቸው ይህንኑ ሁኔታ እንዲያስረዱ ታቅዶ የተደረገ መሆኑን በዝርዝር አስረድቷል።

በሰሜን የአየር ኃይል ምድብ ኃላፊ የትግራይ ተወላጅ የሆነው በሻለቃ ኢሳያስ ሞገስ የሚመራው ይኸው የአየር ኃይል የመኮንኖች ቡድን ከፍተኛ ገንዘብ ከመከላከያ ወጪ ተደርጐ ምግባቸውን እና የቀን ውሎ አበላቸው የተሸፈነ ሲሆን፣ ይህ በዚህ የአየር ኃይል ክፍል የተጀመረው የመዝናኛና የማዘናጊያ ፕሮግራም ወደ ሌሎችም ክፍሎች ቀጣይ እንደሆነ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል።

በምድር ጦር ውስጥ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ እየተነሳ ያለው የጦሩ ጥያቄ እጅግ ያስደነገጣቸው የወያኔ ባለሥልጣናት በአግባቡ ምላሽ ከመስጠት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ይልቅ በሕዝብ ገንዘብና ንብረት የታጠቀውን ኃይል ለማንበርከክና ጥያቄውን እንዳያነሳ ለማድረግ ሩጫ መጀመሩን የገለፁት የመከላከያ ምንጮቻችን ከዚህ ውስጥ ባለፈው ሳምንት በሰሜን እዝ ፈንቅል እና ጉና ክፍለ ጦሮች በተባሉ የጦር ክፍሎች ውስጥ የሚገኙትን የሠራዊቱ አባላት ለማጃጃል ለጥቂት ወታደሮች የቴሌቭዥንና የሬዲዮ ሽልማት በመስጠት ተጀምሮ የነበረ ሲሆን፣ ከነሱ ቀጥሎ ደግሞ የአየር ኃይል መኮንኖችን ለመያዝ ይህን የመሰለ ሽርሽርና አበል እንደተከፈላቸው ለማወቅ ተችሏል ሲሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ባለሥልጣት የጦሩን ጥያቄ ለማዳፈን ከሚያደርጉት ሩጫ በተጓዳኝ ወታደራዊ ውጥረቱ በሁሉም አቅጣጫ የጀመረ በመሆኑ ወያኔ ያለውን አቅም ሁሉ ለመጠቀም እየተሯሯጠ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች እየታዩ ናቸው ሲሉ የመከላከያ ምንጮች ገለፁ።

በዚህም መሠረት ለወራት ያህል ወታደራዊ ስልጠና ሲወስዱ የነበሩት እጩ መኮንኖች ሰሞኑን የፍላግ ማዕረግ እንደተሰጣቸው ምንጮቹ ገልፀው ፍላጉን ሜ/ጀ/ል ታደሰ ወረደ እንደሰጣቸውም ምንጮቹ ገልፀዋል። «ሀገር ሠላም ነው» እያለ ጦሩን ሁሉ እያጃጃለ ያለው ወያኔ ሠራዊቱ ሀገር ሠላም ከሆነ ያለው ሠራዊት በቂ አይደለም ወይ? በማለት በጥያቄ እያጣደፈው ባለበት በዚህ ወቅት በተለያዩ የጦር ካምፖች ውስጥ እያሰለጠናቸው ያሉትን የሠራዊት አባላት እያስመረቀ ወደ ሰሜን እና ወደ ምስራቅ ግንባር እየሸኘ መሆኑን ከአንድ ወር በፊት በሆለታ የጦር ትምህርት ቤት ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ ያላቸውን መኮንኖች አስመርቆ ወደየጦሩ ክፍል የበተናቸው ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ለወራት ያህል የወታደራዊ ስልጠና የተከታተሉ ከ1ሺህ በላይ የሚሆኑ ዕጩ መኮንኖችን የፍላግ ማዕረግ በዚህ በሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ውስጥ እንደተሰጣቸው አስረድተዋል።

እንዲህ ባለ የሠራዊት ብዛት ሕዝቡን ለመቆጣጠር እየተሯሯጠ ያለው ወያኔ ሰሞኑን ደግሞ የትግራይ ወጣቶችን እያፈሰ ወደ እስር ቤት እያጉረ መሆኑን ከመቀሌና አካባቢዋ የመጡ ምንጮች አጋለጡ።

ወያኔዎች በአካባቢው በትግራይ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ተቃዋሚ ድርጅት ስላለ ወጣቱም ወደዚህ ድርጅት ሊገባ ነው በሚል ፍራቻ ብቻ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ወጣቶችን እያፈሱ ለእስር እየዳረጉ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በተለይ በማይጨው ከተማ ውስጥ በሚገኝ በአንድ እስር ቤት ውስጥ ብቻ ከ6ሺህ በላይ ወጣቶች ታስረው እንደሚገኙ አጋልጠዋል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በሽሬ፣ በአክሱምና በመቀሌ እስር ቤቶችም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በርካታ ወጣቶች ታስረው እንደሚገኙ የገለፁት ምንጮች በተለይ መቀሌ ከተማ ውስጥ ድብቅ እስር ቤት እንዳለም አጋልጠዋል:: ይህ ድብቅ እስር ቤት በፖለቲካና በመሳሰሉት ምክንያት በወያኔ ባለሥልጣናት ትዕዛዝ የሚታሰሩት ከመሀል ሀገር ተወስደው ሊታጐሩበት ታስቦ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሰራ መሆኑንም ምንጮቹ ሳይጠቅሱ አላለፉም::

በአሁኑ ሰዓት በትግራይ ባሉ እስር ቤቶች ውስጥ እስረኛ ከመብዛቱ የተነሳ አንዱ በአንዱ ላይ እየተደራረበ ከመሆኑም ባሻገር በርካታ ወጣቶች በታይፎይድና በመሳሰሉት በሽታ እየተሰቃዩ እንደሚገኙም ምንጮች የአይን እማኝነታቸውን ሰጥተዋል::

በሱማሊያ ውክልና ይዞ የገባው የወያኔ ጦር ላይ በየቀኑ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ሲሆን፣ በተጓዳኝ ምንም አይነት መሣሪያ ባልታጠቁ ንፁህ ዜጐች ላይ አፀፋዊ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ በይፋ እየተዘገበ ይገኛል::

ለቀድሞው የዚያድባሬ መንግስት ከፍተኛ መከንን እገዛ ለማድረግ ጦሩን እያስጨረሰ ያለው የወያኔ ቡድን በተደጋጋሚ በጦሩ ላይ በደረሰ ጉዳትና እየደረሰ ባለው ከፍተኛ አደጋ ምክንያት ጅምላ ጭፍጨፋ እንዲፈፅም ከወያኔ ቡድን ትዕዛዝ በመሰጠቱ የተነሳ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንፁህ ሱማሌያውያን በተወለዱበትና እትብታቸው በተቀበረበት ቀዬ ለጥይት ሲሳይ እየተዳረጉ መሆኑን በየጊዜው እየተዘገበ ይገኛል::

በ1969 ዓ.ም. የዚያድባሬ መንግስት «ታላቂቷን ሰማሊያ» ለመመሥረት ካለው ህልም የተነሳ ቀኝ እጅ ናቸው ብሎ ባመነባቸው ከፍተኛ መከንኖች በእነ ኮሎኔል አብዱላሂ ዩሱፍ አማካኝነት የኢትዮጵያን ግዛት ዘልቀው በርካታ ንፁህ ኢትየጵያውያንን ገድለው በርካታ ቦታዎችን ለመቆጣጠር የቻለ

በሶማሊያ ጦርነት በተለይም ባይደዋ ጀምረው እስከ ሞቃዲሾ ድረስ ሲዋጉ የሞቱት የወያኔ ወታደሮች ለቤተሰቦቻቸው መርዶ መነገር መጀመሩ ታወቀ::

ወደ ሱማሊያ ገብተው በማያገባቸው ጦርነት ውስጥ ገብተው ለሞቱት ወታደሮች ለቤተሰቦቻቸው መርዶ እየተነገረ ከመሆኑም ባሻገር ከ5ሺህ እስከ 8ሺህ ብር የደም ካሣ እየተባለ እየተሰጣቸው መሆኑ ታውቋል::

ተዘዋዋሪ የዜና ዘጋቢያችን የሚች ቤተሰብን እንዳነጋገረው ከሆነ ምንም ማዕረግ ለሌላቸው ሟች ወታደሮች 5ሺህ ብር የደም ካሣ የተሰጣቸው ሲሆን ከምክትል አስር አለቃና ከዚያም በላይ ለሆኑት ሟች ቤተሰቦች ደግሞ 8ሺህ ብር እንደሚሰጣቸው ለማረጋገጥ ችሏል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዛሬ በሱማሊያ የሽግግር መንግስቱን ፕሬዝዳንት ሥልጣን ላይ ለማቆየት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሎ በየቀኑ ከ5-10 ወታደሮች እየሞቱ ያሉ ሲሆን፣ ከዛሬ 30 ዓመት በፊት የሱማሊያን ጦር እየመራ የመጣው ይኸው አብዱላሂ ዩሱፍ የተባለው ግለሰብ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሲገድልና ቤት ንብረታቸውን ሲያወድም የነበረ መሆኑን አውስተው አሁንም በዚያን ጊዜ ካደረገው የግፍ ተግባር ባልተናነሰ መልኩ በነመለስ ደጋፊነት ጦሩን እያስገደለውና እያስጨፈጨፈው መሆኑ ያሳዝናል ሲሉ በቁጭት አስተያየታቸው የሚሰጡ በርካቶች ናቸው::

በተያያዘ ከተለያዩ የጦር ክፍሎች «መሞት የለባቸውም» ተብለው ከየግንባሩ ተመርጠው የመጡ የወያኔ ወታደሮች ፍቼ ካምፕ ሰፍረው የፖለቲካ ትምህርት እየተሰጣቸው ሲሆን፣ የፍቼ ከተማን ሕዝብ እየማረሩት መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ይኸው የወያኔ ጦር ከካምፑ እየወጣ ሕዝቡን እየደበደ እና ልጃገረዶችን አስገድዶ እየደፈረ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ሕዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም. 04 ቀበሌ ውስጥ የሚገኙትን የከተማዋ ነዋሪዎች በመሣሪያ እያስፈራሩ በዱላ የደበደቧቸው መሆኑንም አስረድተዋል::

ህዳር 15 ቀን 2000 ዓ.ም. ደግሞ በቀን ስራ ላይ እየተዳደረ የሚገኘውን መስፍን የተባለ የከተማዋ ወጣት የወያኔ ወታደሮች በቦክስ ደብድበው የገደሉት ሲሆን፣ የከተማዋ ሕዝብም በማግስቱ ሕዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም. ገዳይ ወታደሩን በጩቤ ወግተው የገደሉት ከመሆኑም በተጨማሪ አንድ ሌላ ወታደር ማቁሰላቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

እብሪታቸው ያልበረደላቸው የወያኔ ወታደሮች በተደጋጋሚ ጊዜ በከተማው አስተዳደርና በፖሊስ ኃላፊው ጭምር ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ደብዳቤ ቢፃፍላቸውም የተፃፈላቸውን ማስጠንቀቂያ ከምንም ባለመቁጠር ታህሳስ 9ቀን 2000 ዓ.ም. ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ በፍቼ ከተማ ኩማንዶ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ፖሊሱን በቦክስ ሲደበድቡ የተመለከተ የተደብዳቢ ጓደኛ ፖሊስ በጥይት አንዱን ወታደር የዘረገፈው ሲሆን ወታደሩ በአሁኑ ሰዓት በመኖርና በመሞት መካከል በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ተኝቶ እንደሚገኝ የደረሰን ዘገባ አስድረቷል::

በተለይም ሕዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ሳይክል ሲያሽከረክር የነበረ አንድ ወታደር ከፍቼ ወደ አዲስአበባ 27 ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ የነበረ ጐሽ መለስተኛና አነስተኛ የትራንስፖርት ማህበር አርማ የለጠፈ ሎንችን ውስጥ ከነሚያሽከረክረው ሳይክል በመግባቱ ሕይወቱ ወዲያው ሊያልፍ እንደቻለ የጠቆመው ዘገባ ሹፌሩን ወታደሮቹ ከመግደል ባልተናነሰ ሁኔታ የደበደቡት ሲሆን፣ ተሳፍረው የነበሩት ሰዎችም



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለማስጣል ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ቢሆንም ሕዝብን ከመጤፍ የማይቆጥሩት የወያኔ ወታደሮች የተሳፋሪውን ልመናና የሹፌሩን የአስጥሉኝ ጩኸት ወደጐን ትተው ደብድበው ጥለውት እንደሄዱ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

በፍቼ ጦር ካምፕ ውስጥ ሰፍሮ ያለው የወያኔ ቅልብ ጦር የፍቼንና የአካባቢዋን ነዋሪዎች እየደበደበ በማስቸገሩ በአሁኑ ወቅት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ አንድም ሰው በከተማው የማይታይ ከመሆኑም ባሻገር መብራት አብርቶ እቤት ውስጥ ለመቀመጥ በፍርሐት እንደሆነ የደረሰን ሪፖርት ገልፆ በተለይም ሴት ልጃገረዶችን አስገድደው በመድፈር ተማሪዎች የማታ ትምህርት ለመማር እንደተቸገሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሀገሪቱን አርሶ አደሮች እንዲቆጣጠሩላቸው ከየመንደሩ አንዳንድ ገበሬዎች መርጠው «ተሸላሚ ናቸው» በሚል ከኦሮሚያ ክልል ብቻ 500 ገበሬዎችን በሆለታ በማሰባሰብ ድል ያለ ድግስ እንደተዘጋጀላቸው ታወቀ፡፡

ከታህሳስ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ለተከታታይ 7 ቀናት የሚቆየው ይኸው ዝግጅት አምስት መቶ ገበሬዎችን ያቀፈ ሲሆን፣ በየቀኑ ለእያንዳንዱ ገበሬ ለምግብ ብቻ 90 ብር ተመድቦላቸው ለመኝታና ለአበል ከ100 ብር በላይ እየተሰጣቸው እንደሚገኝ የገለፀው የደረሰን ዘገባ በተለይም እነኚህ ተመርጠው የመጡ ገበሬዎች ለእያንዳንዳቸው የማታለያና የመሸንገያ ሜዳልያ ሽልማት እንደሚሰጣቸውም ዘግቧል፡፡

ለገበሬዎቹ የሚውል ገንዘብ በኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አባዱላ ገመዳ ትዕዛዝ ወጪ የተደረገ ሲሆን፣ በቀን በአማካኝ 125 ሺህ ብር የሚወጣ ሲሆን በአጠቃላይ ለ7 ቀናት ብቻ 900 ሺህ ብር ያህል እንደሚባክንም ዘገባው ጨምሮ ገልጿል፡፡

ዛሬ በርካታ የሀገሪቱ ገበሬዎች የግብር እዳ እና የማዳበሪያ ዋጋ የሚከፍሉት ገንዘብ አጥተው ከብቶቻቸውን ከበረት አሟጥጠው ሸጠው ለስደት እና ለልመና እየተዳረጉ ባሉበት በዚህ ወቅት የወያኔ ቡድን ሥልጣኑን ለማራዘም በማሰብ ብቻ ጥቂት አርሶ አደሮችን ከየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ መርጦ በምግብና በአበል እያንበሸበሸ እርስ በርሳቸው በአይነ ቁራኛ እንዲጠባበቁ ለማድረግ ይህን ያህል ብር ወጪ መደረጉ ወያኔ እድሜውን ለማራዘም የሚያደርገው ጥረት መሆኑን ከሚያከናውናቸው ተግባራት መረዳት ይቻላል ሲል ዘገባው አስረድቷል፡፡

በወለጋ ውስጥ ዴዴሳና አካባቢው ለብዙ ዘመናት ሲጠበቅ የቆየውን የደን ሀብት በወያኔ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ትዕዛዝ እንዲጨፈጨፍ መደረጉ ታወቀ፡፡

ከ60 ዓመት በፊት ተተክሎ እስከአሁን በአካባቢው ነዋሪዎች ሲጠበቅ የቆየውን ደን የወያኔ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች «በአካባቢው የተቃዋሚ ኃይል የሚንቀሰቀስበት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ስለሆነ ይቆረጥ» በማለት በአካባቢው የሚገኘው ደን እየተጨፈጨፈ እና በተለይ ዋንዛ እና የመሳሰሉትን እንጨቶች በወታደሩ መኪና እየጫኑ ለጣውላ መሰንጠቂያ ቤቶች እየሸጡ ከመሆኑም በተጨማሪ ለግል ቤቶቻቸውም በሹፌሮቻቸው አማካኝነት እያስገቡ መሆኑን የአካባቢው ተወላጆች በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ሕዳር ወር መጨረሻ ላይ የተጀመረው ይኸው የደን ምንጣሮ የተቃዋሚ ኃይል መንቀሳቀሻ ነው በሚል ለ15 ተከታታይ ቀናት እየተካሄደ ሲሆን በዚሁ ተመሳሳይ ምክንያት ወለጋ ምዕራብ ዞን ጊምቢ ከተማን ጨምሮ ዘጠኝ ወረዳዎች የሞባይልም ሆነ መደበኛ ስልኮች አገልግሎት እንዲያቋርጡ ተደርገው እስከዚህ ሳምንት ድረስ እንዳልጀመሩም የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት እያጋበሱ ለግል ጥቅማቸው እያዋሉት የሚገኙት የወያኔ ቱባ ባለሥልጣናት በየጊዜው የሚዘርፉት ገንዘብ አልበቃ ብሏቸው ዛሬ ደግሞ አለምን እያመሳት የሚገኘው የአየር ለውጥ በኢትዮጵያም እየተከሰተ ከመሆኑም ባሻገር በተለይም 2 ፐርሰንት ብቻ ደን አላት የምትባለው ኢትዮጵያ በወያኔ ከፍተኛ ጦር መኮንኖች እየተጨፈጨፈና ምድረ በዳ እንዲሆን መደረጉ የወያኔ ቡድን ሀገሪቷን ደሀ ከማድረጉ በተጨማሪ ወደበረሀነት ለመለወጥ ቆርጦ የተነሳ መሆኑን ያሳያል ሲሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖች በቁጭት እየገለፁ ይገኛሉ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com